ሰላም ለኢትዮ ፓትርዮት ድህረ ገፅ አዘጋጅ።

ይህን አስተያዬት የምፅፍልህ ከምኖርበት ከሀገረ ሆላንድ ነው።በዚህ ሀገር ለዓመታት ራሱን የነፃው ፕረስ ጋዜጠኛ ብሎ የሚጠራ አንድ ግለሰብ አለ።ይህ ግለሰብ በምንኖርበት ሀገር ፍጹም መሰረት የሌላቸው ወይም ትንሽ ጫፍ ይዞ ቁንጫ የምታክለውን ዝሆን አድርጎ በማቅረብ ይታወቃል።መሰረቱም አሉባልታና ጥላቻ ናቸው።
ታዲያ ይኸው ግለሰብ ሰሞኑን ሰላዮችን እናጋልጥ በሚል እዚህና እዚያ የረገጠ ጭብጥ የጎደለው መርዝ በትኗል። በመሰረተ ሀሳቡ ሰላዮች ካሉ በቂ መረጃ ይዞ ለህግ ማቅረቡ ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ።
ነገር ግን ትግሉ በድህረ ገፅ ወይም በሳይበር ነው ብዬ አላምንም።ለዚያውም
እንደ አቶ ክንፉ አሰፋ ያሉ በአካባቢው ባሉ ህዝባዊ ድርጅቶች በመልካም ስነ ምግባርና ሰብዕና የማይታወቁ ግለሰብ። አቶ ክንፉ አሰፋ የሚታወቁት አንዱን ካንዱ በማጋጨትና የአሉባልታ መርዝ በመርጨት እንጂ በፅናት ቆመው እልህ አስጨራሽ የሆነውን ህዝባዊ ትግል ሲያስተባብሩና ሲመሩ አይደለም።ለዚህ ማረጋገጫ ከፈለጉ ወደ ሆላንድ ስልክ ደውለው የማህበረሰቡን አመራር አባላት ይጠየቁ።

ይልቁንም አቶ ክንፉ የሚታወቁት አዲስ ነገር ብቅ ባለ ቁጥር ቀልጥፈው በመለጠፍ ግን አፍታ ባለመቆየት ሲለዩ ነው።ሁልጊዜ አንደ ትንሽ ልጅት ኩረትን የሚሹ ደካማ ግለሰብ ናቸው።

ትግል ፅናትና ቁርጠኝነት የሚጠይቅ በመሆኑ ለሳቸው አይሆናቸውም፡የሚምታታ ነገር ከሌለ በስተቀር።
በየአካባቢያችን እርሳቸውን የመሰሉ በመካከላችን መተማመን እንዳይኖር
እርስ በርስ እያጋጩ ህዝባዊ ትግሉን የሚያኮስሱትን በቃችሁ እንበል።ህዝብ እውነትን የማወቅ መብት አለው።
ለኛ ይህ ግለሰብ ምንም ይበል ምን ያለው ተዓማኒነቱ ከግምት በታች ነው።የሱን ማንነት ፊት ለፊት የሚሞግቱትን ፊት ለፊት ገጥሞ ማስረዳት ባለመቻሉ መርዙን የሚረጨው በሳይበር ነው። ራሱንም ከሁሉም በላይ አገዝፎ በማየቱ የህዝብ መሰረት ሲያጣ ራሱን ታጋይ አድርጎ በማቅረብ ፀረ- ትግሉ ሀይሎች ጥቃት የሚያደርሱበት መሆኑን ዋይታ ያሰማል።
በሌላ በኩል በየድህረ ገፁ ከሱ የተለዩ አመለካከት ያላቸው ወገኖች እውነቱን እንዳያቀርቡ ቅስቀሳ በማድረግ ህዝብ ጆሮ እንዳይደርስ ጥረት ያደርጋል።
እርሰዎ ይህን አዙሪት ሰብረው ከሱ በተፃራራዊ የሚፃፉ ጽሁፎችን በማቅረበዎ ከልብ አመሰግናለሁ።
በሀገራችን የለም ወይም ተጣሰ የምንለው የሰብዓዊ መብት አካል የሆነው
የፕረስ ነፃነት በመሰል ስደተኞች የሚጣስ ከሆነ ውሃ ቢወቅጡት እንቦጭ ነው። ከጥላቻና አሉባልታ የፀዳ የህዝብን የማወቅ መብት በእውነተኛነትና ሚዛናዊ በሆነ መልኩ የሚያቀርብ ለህዝብና ለሀገር እድገት ከበሬታ ያለው መገናኛ ብዙሀን በማሳደጉ በኩል ለሚያበረክቱት ድርሻ ከልብ በድጋሚ አመሰግናለሁ።

ይታያል በላቸው
ከሆላንድ